## 'ብዙ ዐየሁ' ጥቂቱን ጻፍኩ?

'ብዙ ዐየሁ፤ የህይወቴ ታሪክና ትዝታ' በሚል ስያሜ የተጻፈውን መጽሐፍ እንዲሁም መጽሐፉን በመንተራስ የቀረቡትን ግምገማዎች ተመልክቻለሁ። የዚህ ጹሁፍ ዓላማም የዳሰሳ 'ግምገማ' ለመስጠት ነው።

ለጸሐፊውም ለገምጋሚዎቹም ምስጋናዬን አቀርባለሁ። አቶ ታደሰ ያሳለፈውን ሙያዊ (Professional) ገጠመኞችን እንዲሁም ግለሰባዊ (P?ersonal) ሂደቶችን (ከአንቀልባ እስከ……….) በተሳካለት አማርኛ በመጽሐፋቸው አብራርተውታል።

የኔ ትኩረት 'በተጻፈው' ላይ ሳይሆን መጻፍ ሲገባው ሳይጠቀሱ የታለፉ፤ያልተብራሩ ጉዳዮች ላይ ማተኮር ነው። ኦቶባዮዮግራፊ ሲጻፍ ሁለት አይነት ስህተት የመፈጸም አዝማሚያ ይታያል። Error of Commission (በድፍረት ይሁንብኝ) ተብሎ የሚጻፍ እና የሚነበብ። በወደርነቱ አቻነት በማይተናነስ መልኩ (Error of Omission) መገለጽ ሲገባቸው ያልተገለጹ፤ በአንድም ሆነ በሌላ መልክ ያልተነሱ ስህተቶችን ይመለከታል። አውቀው በድፍረት ይሁንብኝ ተብሎ 'በገጠመኝ' መልክ በኦቶባዮግራፊ ውስጥ ለቀረበው የሚመለከታቸው መልስ እንደሚሰጡበት እርግጠኛ ነኝ። እኔ ግን በአብዛኛው መጻፍ ሲገባቸው ባልተጻፉት 'ብዙ ዐይተው" ባልተተረኩት ላይ አተኩራለሁ።

የግለሰብ ህይወት ቅርጽ የሚይዘው በግለሰቡ እና  በአካባቢው (የቤተሰብ፣ትምህርት ቤት ወዘተ) በሚያጋጥሙ የሶሻል፤ ፖለቲካል  እንዲሁም ኤኮኖሚያዊ ግንኙነቶች  ነው የሚለው አጠቃላይ አንድምታ እንደተጠበቀ ሆኖ አንድ ወጣት እድሜው ለሥራ በሚደርስበት ጊዜ 'እኔነቱ' በየወቅቱ በሚመርጠው የሞራል ውሳኔ እርከን ላይ ይንጠለጠላል። በጣም እጅግ ከበዙት ከዕድሜ ጋር ከሚያጋጥሙ ግጭቶች በተጨማሪ የኤቲክስ ግጭቶች በየወቅቱ ይነሳሉ። እነዚህ የኤቲክስ ግጭቶችም በአብዛኛው ሙያንና ግለሰባዊ የሞራል መዋቅርን መሰረት ያደረጉ ናቸው። እነዚህ ግጭቶች በአብዛኛው የሚጠናቀቁት በአንዱ ወይም በሌላው አንጻራዊ ጥንካሬ ነው። 'እናቴን ያገባ ሁሉ አባቴ ነው' በሚል ብሂል ላይ የሚሽከረከር የግለሰብ ሞራላዊ መዋቅር ለማንም ለምንም ለመነጠፍ ጊዜ አይወስድበትም። አንዱ የሞራል ግጭቶችን ማስታረቂያ መንገድ ስለሆነም ጭምር። የኑሮአቸውን ዘይቤ፣አካሄድ በዚህ  መሰል ሞራላዊ ምህዳር ላይ የሚሽከረከር ግለሰቦች ለሂትለር፣ለስታሊን እንዲሁም ዛሬ በህይወት ለሚገኙ አምባገነኖች ቀን ከሌት ሳይታክታቸው ሲያገለግሉ ይታያሉ። አገልግሎታቸውን በታላቅ የሞራል ሞራ በመሸፈን፤ በመሸሸግ 'የምናገለግለው ሕዝባችንና አገራችንን" ነው ሲሉም ይደመጣል፤ ሲጽፉም ይነበባሉ። እነዚህን መሰል ግለሰቦች በመሪነት የተቀበሉትን ግለሰብ፤ አባል የሆኑበትን የፖለቲካ ድርጅት 'ታላቅ ተልዕኮ" በአርቆ አሳቢነት በመረዳት፤ ትርፍና ኪሳራውን በማመዛዘን፤ የሚስበውን ጦስ በመረዳት አልገቡም ብሎ ለሚከራከር የስታሊንና የሂትለር ዘመን ምሁራንን ለማመሳከሪያ መጥቀስ በቂ ይሆናል።

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

ወደ መጽሐፉ ስንመለስ አቶ ታደሰ በአካባቢያቸው ያለፉበትን ታሪካዊ ክስተቶች ሳያነሱ፣ ሳያጣቅሱ በአብዛኛው አልፈውታል። በወቅቱ በኢትዮጵያ ውስጥ የኖረ ሰው የቀይ ሽብርን ክስተት በኦቶባዮግራፊ ውስጥ ካለነሳ ያ ግለሰብ 'በተፋለጠ የእኔነት መዋቀር' የተገረፈ ያም ካልሆነ ጸላጦስዊ እጅን መታጠብ ዘይቤን እንጀራዬ ብሎ የያዘ ብቻ መሆን ይኖርበታል።ምክንያቱም በወቅቱ ከተሰራው አጸያፊ ድርጊት ራስን ለማግለል 'ከደሙ ንጹህ" ነኝ በሚል ከነባራዊ ሁነታ ለመሸሽ በሚወሰድ እርምጃ - በማወቅም ሆነ ባለማወቅ። ሳይኮሎጂስቶቹ ይህን መሰል ከዕውነት ሽሽቶ መደናበር 'Denial" ይሉታል። ከባንክ ተወሰደው የተገደሉ፣የታሰሩ፣የተገረፉ፣ ዋናው ባንክ ደጃፍ ላይ ሬሳቸው ተጥሎ ተራምደን ያለፍናቸው የሉም ካልተባለ በስተቀር። ሆድ ከአገር ከሰፋም ወጣት የጉራጌ ወጣቶቹን የፈጀውን 'ሺህ ገዳይ' ሳይነሳ መታለፉ ለምን ይሆን። አቶ ታደሰ በግፍ የተገደሉት ወጣቶች በቀላሉ ከብሔራዊ አካውንት ሌጀር ላይ ሊፋቁ አይችሉም፣ ክቡር የሰው ልጆች ናቸውና!!

ይሄም በኦቶባዮግራፊዎ ትረካ ውስጥ አርእስት የማይጨብጥ ጉዳይ ቢሆን በየወቅቱ ሰለሚዘረፉት ባንኮች እንዴት በሙያዊ ይመለከተኛል እሳቤ 'ውሃ ሳይቋጥሩ" ቀሩ። በአንጻሩ የብር ኖቶችን አስመልክቶ ስለ ሁመራ ባንክ በዝርዝር ሲተረክ ማለቴ ነው።

አቶ ታደሰ ኢሠፓ የአጥፊዎች ክምችት ነው። ድርጅቱ ወንጀለኛ ይሁን አይሁን ታሪክ ፍርዱን ይሰጣል፣ ጥፋቱን ግን ማንም የሚስተው አይሆንም። የድርጅቱ አባላትም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ አብረው ከተቧደኗቸው አጥፊዎች ጋር 'ጥፋቱን' በጋራ ካለሆነም በጋራ 'ፀፀቱን' መረከብ ይኖርባቸዋል። ግለሰብ የድርጅቱ አባላቶቹ የጥፋት ድርጊቱን በቀጥታ ይፈጽሙትም አይፈጽሙትም። በናዚ ጀርመን አብዛኛውን አይሁዶችን 'የማስወገድ ስራ' በሙሉ ልብነት ይፈጽሙ/ያስፈጽሙ የነበሩት የመንግስት ቢሮክራቶች እንደነበሩ ማስታውስ በአገራችን በወቅቱ የነበረውን ሁኔታ ይበልጥ ግልጥ ያደርገዋል። ችግሩ በናዚ ጀርመን እንደነበረው አብዛኛው ቴክኖክራቶች "ግልጋሎቴ ለአገሬ" ነው በሚል ካባ ስለሚንቀሳቀሱ የግለሰቦቹን የስልጣን ጥም በግልጽ እንዳንመለከት ይጋርደናል። እውነት ለሐቅ አቶ ታደስ የስልጣን ጥም ካልሆነ በስተቀር ከገዳይ አገር አጥፊ ጋር አብሮ መስራት፣ ተለማምጦ ማደርን ምን አመጣው? ከዩንቨርስቲ ጀምሮ በደራሲው ላይ የተንጸባረቀውን ራስን የመውደድ በባህርይ (በወቅቱ ተመራቂ የነበሩ ተማሪዎች ቦይኮት ሲያደረጉ ደራሲው በአንድም ሆነ ሌላም ምክንያት ማጠናቀቃቸው) ቀጣይ በሆነ መልኩ ወንጀለኛ ለሆነ መሪ (ያውም ሆድ በሚያባባ አጻጻፍ "ካናቴራው ለተቀደደ" አገር ወዳድ) ተነጥፎ ማገልገል ህሊናው ከበለዘ ቴክኖክራት የሚጠበቅ ካለሆነ በስተቀር ከሐቀኛ ምሁር የሚታሰብ አይሆንም። ወቅቱ ከአውሮፓ ከአሜሪካ እንዲሁም ከሌሎችም ቦታዎች ለዲሞክራሲ ለሚደረገው ትግል ምሁራን በጸረ ደርግ ሰልፍ የሚቀላቀሉበት ጊዜ መሆኑ በአንጻሩ ጸሐፊው ለስርዓቱ ታማኝ አገልጋይ የመሆን ምርጫ የ'ድርሰቱ"ን ነባራዊነት የሐቅ ጠላት ያጠላበታል።'ስታይሌ' ነው ካልተባለ በስተቀር።

አቶ ታደሰ በኦቶባዮግራፊ ማህደራቸው ውስጥ በፓርቲያቸው ውስጥ ሲካሄድ የነበረውን ሽኩቻ አባል ከመሆናቸውም በፊት ሆነ ኋላ ትኩረት ለምን እንዳልሰጡት እስከሁን ግራ ይገባኛል። የ60 ዎቹ መረሸን፣ የነጀነራል ተፈሪ ባንቲ የነ ሻለቃ አጥናፉ መገደል፣ የግንቦት ወሩ የመፈንቅለ መንግስት ሙከራ ወዘተ ትኩረታቸውን አልሳበውም።ይበልጥኑ መጽሐፉ

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

ያተኮረው ጥቃቅን በሆኑ ክስተቶች፣ አንድምታቸው ከግለሰቡ ሳኮሎጂካዊ ምህዳር መጥቀው በማይልፉ ጉዳዮች ላይ መሆኑ የ 'ኦቶባዮግራፊዊን' ሙላት ከወዲሁ ቀንሶበታል።

በአገራችን ኢትዮጵያ ብቅ እያሉ ከምናነባቸው ኦቶባዮግራፊዎች አንጻር መንተራሻ ሊሆኑ የሚችሉ መጻህፎች ለአቶ ታደሰ ኦቶባዮግራፊ መገምገሚያ መነሻ ሊሆኑ ይችላሉ። የአቶ ተፈራ ደግፌ 'Tripping Stone' የ የፌታውራሪ ተክለ ሃዋርያት 'ኦቶባዮግራፊ'፣የነጋ መዝለቂያ (Notes from the Hyena's Belly) የአብዶሽ አቦኝ 'በርጫ' ወዘተ። የአብዶሽ ጹሑፍ "የተዋጣለት" ተብሎ ሊሰየም የሚበቃ ጸሁፍ ነው። በአንጻሩ የነጋን መድበል (Notes from a pervert) ብሎ ቢሰየም በተገባ ነበር። አቶ ተፈራ ደግፌ በኦቶባዮግራፊያቸው የእስር ቤት ሰቆቃቸውን በሚመለከት በአንጠልጣይ አጻጻፍ ዘይቤ ለአንባብያን አቅርበዋል። የደርግ የአስር ቤት ዘመን፣ የሥርዓቱን አስከፊ ገጽታ ለመጭው ትውልድ ምስክርነታቸውን አቅርበውልናል።አቶ ተፈራ ደግፌ በማያዉቁት ምክንያት 'የጽልመት ካባ ተላብሰው' ከስልጣናቸው ወደ ወህኒ ቤት ሲወረዱ በአንጻሩ አቶ ታደሰ 'በፈገግታ' ቦታቸውን ወርሰው 'አገራዊ' ግዴታቸውን ተወጥተዋል። ፊታውራሪ ተክለ ሐዋርያትም አገራችንን የገጠማትን አስተዳደር፣የትምህርት ዘመናቸውን፣ እምቢ ባይነታቸውን በሰፊው ገልጸውታል። የፊውዳሉን መንግስት ከማገለገል 'በሙያቸው' በግላቸው መተዳደርን መምረጣቸውን ከኦቶባዮግራፊያቸው እናነባለን። ጥያቄው ህሊናን አደንዝዞ ስብዕናን በሚገፍ መንግስት ውስጥ ማገልገል ወይስ በግል መተዳደር (እንደ ፊታውራሪ ተክለ ሐዋርያት) ካልሆነም ወህኒን መምረጥ (እንደ ተፈራ ደግፌ) ነው። የመጀመሪያዎቹ ሁለቱ ኦቶባዮግራፈሮች የመጨረሻውን አማራጭ ሲቀበሉ አቶ ታደሰ በታማኝነት እና 'በቅንነት' 'የአገር ወዳጁን' መንግስት ሲያገለግሉ ቆይተው ከባለ 'ቀዳዳ ካናቴራ' መሪያቸው ጋር አብረው ተወግደዋል። ይሂ እውነት ነው ግን ዳግም ጥያቄው አቶ ታደሰ ናቸው አገራቸውን ያገለገሉ ወይስ ፊታውራሪ ተክለ ሐዋርያት እና አቶ ተፈራ ደግፌ? አቶ ታደሰ ለዚህ ጥያቄ የሚሰጡትን መልስ ባውቅ (ከወዲሁ መገመት ብችልም) በአሁኑ ወቅት ወያኔን በማገልገል ላይ የሚገኙትን አይቶ ተክለወልድ አጥናፉ እና አይቶ ግርማ ብሩ ማንን እያገለገሉ እንዳሉ ቢነግሩን መልካም ይሆናል።

አቶ ታደሰ ለሚሾሙበት ቦታ ቅድሚያ መረጃ እንደሌላቸው ደጋግመው ሲጽፉ ይነበባል። ለባንክ ገዥነት፣ለውጭ ንግድ ሚንስቴርነት፣ለፓርቲ አባልነት፣ ለአምባሳደርነት ከሳቸው ዕውቅና ውጭ ድንገት 'ሰበር ዜና' ሆኖ እንደሚሰሙት ደጋግመው ነገረውናል። በደርግ ዘመን ይፈለጉ የነበሩ 'አገልጋይ ምሁራን' ፕሮፋይል ባናውቀው ኖሮ እጅግም አይገርመኝም ነበር። ግና በ'ሰበር ዜና" ተደጋግሞ ሹመት ሲሰጥ ይገርማል ከማለት በስተቀር ምንም ማለት አይቻልም። ምናልባት ያልተጻፈ 'ነገር' ካለ በሚል ነው ያነሳሁት። 'በእንዝህላልነት' እንዳላማቸው አቶ ታደሰ የልጅነታቸውን ጊዜ ቁልጭ ባለ መልክ የሚያስታውሱ ስለሆነ 'ከባለቤቱ ያወቀ ቡዳ ነው' ያሰኛልና በዚሁ እተወዋለሁ። ነገር ግን በባዮግራፊያቸው ውስጥ ደራሲው እራሳቸውን ምንጊዜም በሐቅ መንገድ ላይ የቆሙ ፣ ፊሽካ ነፊ፣ Hero ሌሎቹ ባንጻሩ villain፣ ስግብግብ፣ለአገር ለወገን የማያስቡ ሆነው መቅረባቸው ሚዛናዊ ትንተናውን ያዳፋዋል የሚል ግምት አለኝ።ቢያንስ ቢይንስ ሌላው ወገን የሚለውን እስከማነብ ድረስ።

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

አቶ ታደሰ በደርግ ጊዜ አንድ የዩንቨርስቲ ምሩቅ ደሞዝ ከ ብር 500 አይዘልም። ከዚህም ውስጥ ለ'እናት አገር" ጥሪ 'ለመደበኛ ልብስ" ማሰፊያ እየተባለ ከገኘሮዎች በሚወርደው ቀጭን ትዕዛዝ ተቀናንሳ በ'እጅ' የምትደርሰው ከብር 300 አትበልጥም። ይች ብር 300 ለቤት ኪራይ፤ለምግብ፤ለታክሲ እንዲሁም ለልዩ ልዩ ወጭዎች የምትሆነው። 'የአሳ ግማቱ ከጭንቅላቱ" መሆኑ ተዘንግቶ የሥራ ጊዜ አይከበርም ብሎ ሠራተኛውን መክሰስ ተገቢ ነው? ጊዜው የህብረተሰብ መዋቅር በተሰባበረበት ወቅት፤ አኖሚክ ሁኔታ በሰፈነበት ጊዜ ከሰራተኛው ምርታማነትን መጠበቅ ተገቢ አይመስለኝም። ያውም ለወታደራዊና ሲቪል ቢሮክራቶች ፈቃድ ላይ በተሰማራ የሚንስቴር 'መዋያ' ቤት።

አቶ ታደሰ በዝርዝር ያጋጠማቸውን ሲያጫውቱን በመጨረሻ ያገለግሉበት በነበረው በኦታዋ ቢሮአቸው ገጠመኞቻቸውን በዝርዝር ሳያነሱት አልፈውታል። 'ዝርዝር ኪስ ይቀዳል' ካልተባለ በስተቀር። ተቃዋሚዎች በበርካታ ቁጥር በኦንታሪዮ እንዲሁም በሌሎች የካናዳ ክፍላተ ሐገሮች እንደሚገኙ እገምታለሁ። እውነት ለሐቅ የተቃዋሚዎችን እንቅስቃሴ ለውጭ ጉዳይ ሚንስቴር ወይም ለሚመለከተው ክፍል ሪፓርት አይደረግም ነበር? እውነት ለሐቅ ፓስፓርት ለማሳደስ ቢሮዎ ድረስ ተመላላልሰው ሳይሳካላቸው የተመለሱ የሉም?

አቶ ታደሰ ይህን ሁሉ ዝባዝንኬ ወጥ ባልሆነ መንገድ ያቀረብኩት ኦቶባዮግራፊዎ 'የተሟላ" ብሎም 'የተዋጣለት" እንዲሆን በማሰብ ነው። በአሁኑ ደረጃ ግን ብዙ ይቀረዋል። በመጨረሻ ባለቅኔው ጸጋዬ ትንሽ 'ስኳሩ' ከፍ ብላበት ወይም በአንጻሩ የProse ችሎታዎን በወቅቱ ሳያሳዩት ቀርተው ይሆናል እንጅ በመድብሉ ውስጥ ያነበብኳቸውን ግጥምች ቢያነባቸው ኖሮ የግጥም ችሎታዎትን ጥያቄ ውስጥ እንደሚከተው፤ የ prose ችሎታዎትን እንደሚያደንቀው ከወዲሁ አልጠራጠርም።

አመሰግናለሁ

ጋምቢ

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com